# ቢያፈቅሩት ወይስ ቢንቁት?

ከዘነበ በቀለ

የኢትዮጵያ ፖለቲካ ፓርቲዎችና ድርጅቶች መሰረታችን አገር ቤት ነው ይበሉ እንጂ! በሀገር ውስጥ የሚገኘውን ቀጥተኛ የሀገሩ ተጠሪ የሆነ ህዝብ እየተዉና ወደውጭው አገር ነዋሪ ኢትዮጵያዊ ዘንድ እየፈረጠጡ መምጣትን እየተላመዱት መሆኑ እየተስተዋለ ነው። ምክንያቱ ምን እንደሆን ባይገባም ለምርጫው የሚቀሰቀሰው የመምረጥ ዕድል የሌለው የዲያስፖራ ነዋሪ መሆኑ የሚያስገርም የፖለቲካ ቅየሳ ነው። ይህ አይነቱ ተግባር የዲያስፖራውን ጉብል ፖለቲከኞቹ ቢያፈቅሩት ነው ቢንቁት ማሰኘቱ አይቀርም። የጥንቱ ይትበሃል! የዚህ አይነቱን ገጠመኝ " ፍየል ወዲህ ቅዝምዝም ወዲያ" ፤ "የት አውቅህ ብሎ አጥብቆ ሳመኝ"... ወዘተ በሚል ይገልፀዋል።

የኢትዮጵያ ህዝብ ከፖለቲካ ድርጅቶቹ የሚጠብቀው አማራጭ የሆነ የትግል ስልት ቀይሰው እንዲያታግሉት እንጂ! አፋኙንና ጨቋኙን የወያኔ አገዛዝ እንዲለምኑለት፤ እንዲለማመጡለት፤ እንዲያማልዱት፤ አልጠየቀም። ገንዘብ አዋጡልኝና ህዝቡን ለድል ላብቃው በሚል ፈሊጥ የልመና ከረጢታቸውን አዝለው በዲያስፖራው የሚንከራተቱት የፖለቲካ ሰዎች እውን የህዝብ ነፃ አውጭዎች ናቸው እንበል? በአንዳንዱ ሁኔታ ላይ እንኳንስ ሌላውን እራሳቸውንም ከውጭ ተፅዕኖ ነፃ ያላወጡ መሆናቸው እየተስተዋለ ነው። ታዲያ! ለዲያስፖራው ያላቸው ፍቅር ከየት መነጨ ብል አኩራፊ አተርፍ ይሆን? ምንተዳዬ!። በዚህ የነ ፎጠኔዎች ዘመን ላይ ተሆኖ፤ የዋሆች የማይጠረጥሩት ነገር ባይኖር ማን ሊቀየም ይቻለዋል። ዓለም የንግድ ገበያ በሆነችበት በአሁኑ ሰዓት ህዝባዊ የሆነ ሀይማኖትና ሞራል፤ ባህልና ዲሲፕሊን መሰረታቸውን ለቀው ቢፈረጥጡ ኑ! ተመለሱ! እያለ ተከትሎ ልቡ የሚወልቅ ማንም ሞኝ አይኖር። ባይሆን ግን እንደዘመኑ ባይንጮለጮሉ፤ ጠንቃቃ ዜጋ ሆኖ መገኘቱ ያባት መሆኑን የማይረዳ ይኖራል ብዬ አልገምትም። ምርጫው ያለው እዚያው ሀገር ውስጥ፤ መራጩ ያለው እዚያው ሀገር ውስጥ፤ " ምን ከምን ሄዶ ቁርበት አንጥፉልኝ አለ" ብሎ ለመሳለቅ እንኳ ባይደፈር፤ አያ እከሌ! ከቶ ምን ልትፈይድ ብቅ አልክ ወደኛ ዘንድ? ብሎ የሚጠይቅ የዕድሜ ባለፀጋ የተመከሮ ጌታ አለማጋጠሙ፤ ለድርጊቱ መንስኤ ሊሆን መብቃቱን አልጠራጠርም። ቢሆንም ግን ዲያስፖሬው አውቆ ይሞኝ እንደሁ እንጂ! ላለበት ያበቃው አሰለጤነቱ የፈዘዘ የደነዘዘ ነው ለማለት አያስደፍርም።

አንድ ማስፈራራት የለመዱ ሰው አይን ያወጣ ደፋር ገጠማቸውና ጉድ ፈላባቸው። ውጣ ከዚህ ብዬሃለሁ! ብለው በቁጣ ቢያጉረጠርጡም፤ ሰውዬው አልወጣም ምን ትሆናለህ! ብሎ ሲገተርባቸው፤ መጀመሪያ ኮታቸውን፤ ቀጥሎ ከረባታቸውን፤ ቀጥሎ ሸሚዛቸውን እያሉ ከላይ የለበሱትን በሙሉ አውልቀው እስኪጨርሱ ድረስ፤ ጣልቃ እያገቡ አትወጣም? ቆይ ቆየኝ! በማለት ማስፈራራታቸውን አላቋረጡም ነበር። ሰውዬው ግን ከመጤፍ ባለመቁጠር፤ ወደስረኛው የልብሳቸው ክፍል ወደሱሪያቸው እስኪደርሱ ድረስ ዝም አላቸው። እስኪ ምን ልትሆን ነው እያለ ቆሞ ሲያስተውላቸው፤ ሁሉንም ነገር ተዉትና! እንደገና መለባበስ ያዙ። የፖለቲካ ድርጅቶቻችንም አጉል ድንፋታ በወያኔ ደፋርነትና እስኪ ምን ልትሆኑ ነው ባይነት መጠናቸው ቁመታቸው ወርዳቸው እየተለካ መምጣቱ እየታየ ነው። በሰላማዊ ትግል ወያኔን እናሽመደምድዋለን ሲሉን የከረሙት ድርጅቶቻችን፤ ሰላማዊ ትግላቸውን ትተው ህጋዊ ትግል ነው የምናካሂደው ብለው ቢሉም፤ ወያኔ አንጀቱ ስላልሳሳ፤ ድርጅቶቹ ጀግና መስለው ለቀረቡት ህዝብ ስሞታቸውን እያዥጎደጎዱት ነው የሚገኙት። ወያኔ ገደለን! ጨረሰን! እያሉ ሲያወሩ፤ ትንሽ እንኳ ላፋቸው አይቀፋቸውም። ቢያንስ ቢያንስ ሚስቱን

እደበድባለሁ ብሎ የፎከረው አባወራ በሚስቱ ተገልብጦ ሲጠፈጠፍ አረ! ተጋደልን! እያለ ሀፍረቱን ለመሸፈን የጣረውን ሰው ያህል እንኳ! አቻ ለአቻ መሆናቸውን ለመዋሸት ከማይችሉበት ደረጃ ላይ መድረሳቸው ገሀድ ሆኗል። ገንዘብ ቢኖረን ኖሮ ወያኔን በምርጫ እናሸንፈው ነበር የሚሉት ፌዝ ደግሞ አዲስ ታክቲክ መሆኑ ነው። ዲያስፖራው ወያኔን ያሸንፉታል ብሎ አምኖ ገንዘብ እንዲለግስ መጠየቁ፣ ቢፈቀር ወይስ ቢናቅ? መልሱ እንቆቅልሽ ነው።

የኢትዮጵያ ህዝብ ጥንትም ቢሆን በፍከራው፣ በጃሎታው፡-

"የምር ተኳሹን እኛ ስናውቀው፣
ዝናር በቅፌን ማን ደባለቀው።" ብሏል።

ወያኔ ከዲያስፖራ የተሰበሰበ ገንዘብ እንኳንስ ከስልጣን ሊያወርደው ሊያነቃንቀው እንደማይችል የታወቀ ነው። የሀገሪቱን ኤኮኖሚ ሰርቆ በእጁ ያስገባ የሽፍታ ጥርቅም እንዴት አድርጎ ነው በዲያስፖራ መዋጮ ሳቢያ በምርጫ ሊበለጥ የሚችለው? ይልቁንስ! ወያኔን የሚገጠው፣ የሚያስፈራው፣ እንደ ቅጠል የሚያንቀጠቅጠው አንድና አንድ ነገር ብቻ ነው። ያም ህዝባዊ አመፅ። ህዝብ በቃኝ አልገዛም ብሎ መነሳት ሲችል። ለዚህ አይነቱ አመፅ መሰረቱ ህዝባዊ ብሶት ሲሆን በተቀናጀ አመራር አደራጅቶ ለድል ማብቃት ደግሞ የድርጅቶቹ ተግባር ነበር። ታዲያ ድርጅቶቻችን ያንን ነው እያሳዩን ያሉት? ወይስ የገንዘቡ ስብሰባ ፍሬ ቋጥሮ ለድል ያበቃናል ብለን እንዋዛ? ወያኔ የገንዘብ ማጠራቀሚያዋን ማሰሮስ ነጥቆ እንደማይወስዳት ማን ነው ማረጋገጫ ሊሰጥ የሚችል? ነው? ወይስ ገንዘቡም በስደት ሊኖር?

ይኸ ቀልድ ነው። የዚህ አይነቱ ቀልድ ደግሞ የራሱን ጊዜ ወስዶ ተተውኖ አስጨብጭቦም፣ አሳዝኖም አልፏል። በደርግ ጊዜ የደነቆረች አሁንም መንግስቱ ይሙት! እያለች ብትምል ማን ይፈርድባታል። ህክምና ካላገኘች በቀር። እናም! የኢትዮጵያ ህዝብ የመኖርና ያለመኖር ጥያቄ ላይ ነው የሚገኘው። ላዳዲስ ታክቲክ ሰሪዎች የሰርቶ ማሳያ ጣቢያ አይደለም። የኢትዮጵያ ህዝብ በእውነተኛ ስሜትና ፍቅር የተቆራኙትን ጠንቅቆ ያውቃቸዋል። የበላውን በልተው፣ ያደረበትን አድረው፣ የዋለበትን ውለው ሊያደራጁት ሲጥሩ አስተውሏቸዋል። እንጂ! በስሙ ገንዘብ ሲሰበስቡ አይደለም የሚያውቃቸው። ያ! ሀቅ ነው። ለደረሰባቸው ለሚደርስባቸው ሁሉ፣ ከህዝባቸው ጋር ሆነው መከራን ሲወጡት እንጂ! ሞትከ አድነኝ እያሉ! ህዝብን በጩኸት ሲያደነቁሩት አልተስተዋሉም። አብረውት ይራባሉ፣ ይጠማሉ፣ ይታመማሉ፣ ይጎሳቆላሉ፣ ይሰቃያሉ። ይታገላሉ፣ ያታግላሉ፣ አብረውትም ለድል ይበቃሉ። ያ! ነው የፍቅራቸው መወጫ። ያ! ነው የአለኝታነታቸው መገለጫ።

ድል ለኢትዮጵያ ህዝብ!